# መግቢያ

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዓላማ፣ ተግባራትና ኃላፊነት ዙሪያ ለመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ ለመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎችና ለመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አባላት በተዘጋጀው የምክክር አውደጥናት ላይ ለውይይት ለመነሻ እንዲሆን ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ጽሁፉ በአራት ክፍሎች ተዋቅሯል፡፡

በዚሁ መሠረት በክፍል አንድ የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማስፋት ሲባል በዕንባ ጠባቂ ትርጉም፣መለያ ባህሪዎቹና በተለያዩ አገሮች ተሞክሮ ዙሪያ ቅኝት የሚያደርግ ሲሆን ክፍል ሁለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የተቋቋመበትን ምክንያቶች፣ የተቋሙን ዓላማ፣ ኃላፊነት፣ ተግባራት፣ ተቋሙ ከሌሎች የዲሞክራሲ ግንባታ ተቋማት ጋር ያለውን ልዩነትና አንድነት ይተነትናል፡፡ የመልካም አስተዳደር ምንነትና መገለጫዎቹ፣መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚያስፈልጉ የፖሊሲ ድጋፎች፣ መልካም አስተዳደር ለዘለቄዎዊ ልማት ያለው አስተዋጽኦ፣ የመልካም አስተዳደር ተሞክሮ በኢትዮጵያ፣ መልካም አስተዳደርን በኢትዮጵያ ለማስፈን ያጋጠሙ ችግሮች እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን አንጻር የሕዝብ እንባ ጠባቂ ሊኖረው ስለሚገባ ሚና በክፍል ሶስት ተብራርቷል፡፡ በክፍል አራት የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በአዋጅ የተሰጡትን ኃላፊነትና ተግባራት በአግባቡ እንዲወጣ ከመንግስት አስፈጻሚ አካላት፣ ከመገናኛ ብዙሀንና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚጠበቅ ተግባራትን በመዘርዘር ይቋጫል፡፡

## 1. እንባ ጠባቂ ማለት ምን ማለት ነው?

## *1.1 ምንጭና ትርጉም*

በ The Free Encyclopaedia, (2006) መሰረት እንባ ጠባቂ (Ombudsman) የሚለው ቃል የተገኘው Umboosmaor ወይም Umbudsman, ከሚል ጾታን መሠረት ካላደረገ የጥንታዊ Norse ቃል ሲሆን ቃሉ ጠበቃ፣ ወኪል፣ ለውጥ አምጭ ከሚሉት ቃላት ጋር የሚዛመድ ትርጉም አለው፡፡ Ombudsman /እንባ ጠባቂ የሚለው / ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ስራ ላይ የዋለው ስዊዲን አገር ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ቃሉ በተለያዩ ቋንቋዎችና በተለያዩ አገሮች የተለያዩ መጠሪያዎችን ይዞ ተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡

ለምሳሌ የስካኔንዴቪያን አገር የሆነችው አይስላንድ ዕንባጠባቂን በአይስላንደስ ቋንቋ "Umboosmaour", ስትለው ኖርዌይ በበኩሏ በኖሮጂያን ቋንቋ "Ombudsmann" እና ዴንማርክ በዴኒሽ ቋንቋ "Ombudsmand" በማለት ሲጠሩት በሙስሊም አገሮች ደግሞ እንባጠባቂን Qadi.al-Qadat በማለት ይጠሩታል፡፡

የእንባ ጠባቂ (Ombudsman) ትርጉምን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መልኩ ፍቺ የሰጡት ሲሆን ለአብነት ያህል የተወሰኑ ታዋቂ ፀሀፍትና ምሁራን የሰጡዋቸውን ትርጉሞች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

ዴቪስ /1996፡1051-1079/ የተባሉ ምሁር ዕንባ ጠባቂን ሲተረጉሙ፡-

*ዕንባ ጠባቂ ማለት በመንግስት ስልጣን ውስጥ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ የሚቀመጥ ሰው ነው፡፡ ስራውም አስተዳደሩ ላይ ወይም በሲቪል ሰራተኞች ላይ የሚቀርቡትን የማንኛውም ዜጋ ቅሬታዎችን ተቀብሎ መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ ነው በማለት ያስቀመጡ ሲሆን፣*

ጀስቲስ ሪፖርት /1961፡አንቀጽ 2/ ደግሞ እንባ ጠባቂ፡-

*"የፓርላማ ተሿሚ መሆኑንና ተቀዳሚ ተግባሩም የፓርላማ ወኪል ሆኖ በስራ አስፈጻሚው አካል ከሚደርሱት የአስተዳደር በደሎች ዜጎችን መጠበቅ ነው ብሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በርናርድ ፍራንክ /1986፡11/ የተባሉ ፀሀፍት፣ << እንባ ጠባቂ ማለት በህገ መንግስት የተቋቋመ ተቋም ወይም በገለልተኛና ከፍተኛ ስልጣን ባለወ ሰው የሚመራ ህጋዊ ተቋም ነው፡፡ ይህ ገለልተኛ ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለህግ አውጪው አካል ሲሆን በመንግስት መስሪያ ቤቶች ባለስልጣናት እና ሰራተኞች አማካኝነት በደል*

*የተፈጸመባቸው ግለሰቦች ቅሬታዎችን ተቀብሎ የሚያጣራ አካል ነው፡፡ ወይም በራሱ ተነሳሽነት የአስተዳደር በደሎችን መመርመር፣ የማስተካከያ ሃሳብ ማቅረብ እንዲሁም ሪፖርቶችን ማቅረብ ስልጣን ያለው ነው፡፡"* በማለት ሰፋ ያለ ትርጉም ሠጥተውቷል፡፡

የኦክስፎርድ መዝገብ ቃላት ደግሞ " እንባ ጠባቂን" እንደሚከተለው ይተርጉማል፡፡ "እንባ ጠባቂ ማለት በመንግስት የተሾመ ባለስልጣን (ተሿሚ) ሲሆን ተግባሩም ዜጎች በመንግስት ባለስልጣናት ላይ የሚያቀርባቸውን ቅሬታዎችን መርምሮ ሪፖርት ማቅረብ ነው፡፡" በማለት ተርጉሞታል፡፡

ኘሮፌሰር ሮዋት "The Ombudsman: Citizen's Defender "በተሰኘው ታዋቂ መጽሐፋቸው የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡

*"እንባ ጠባቂ ነጻና ከፖለቲካ ተጽዕኖ ገለልተኛ የሆነ የህግ አውጪው አካል ተሿሚ ሲሆን የአስተዳደር ጥፋት ሲፈጸም ከዜጎች የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች የሚመረምር ነው፡፡ እንባ ጠባቂው የአስተዳደር ጥፋት ሲከሰት ድርጊቱን የመተቸት እንዲሁም ጥፋቱን ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ ስልጣን አለው፡፡ነገር ግን ድርጊቱን የመቀልበስ ስልጣን የለውም፡፡"* ( ሮዋት፤ 1986 :1)፡፡

ሎዌንስታይን በተባሉ ምሁር ትርጉም መሠረት ደግሞ፡-
*"እንባ ጠባቂ በፖርላማ የተመረጠ ገለልተኛ ወገን ሲሆን ህዝቡ የአስተዳደር በደል እንዳይፈጸምበት የሚጠብቅ ነው፡፡" (ሎዌንስታይን፤ 1965፡ 403)፡፡*

ኘሮፌሰር ኩቼን /1981፡68/ በበኩላቸው እንባ ጠባቂን እንዲህ በማለት *ተርጉመውታል፡-*
*"የተከበረ <u>የፓለቲ</u> ሰው፣ ከቢሮክራሲ የራቀ እና በመንግስት አገልግሎት ላይ ዜጎች የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች መርምሮ የማስተካከያ ሃሳብ የሚያቀርብ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ እንባ ጠባቂው የአስተዳደር ጥፋቶች ተፈጽመው አቤቱታዎች ሲቀርቡለት እነዛን ጥፋቶች ይመራመራል፣ ይተቻል እንዲሁም እውነታውን ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ ነገር ግን የተፈጸሙትን በደሎች ወይም ውሳኔዎች የመቀልበስ ስልጣን የለውም በማለት አቅርበውታል፡፡*

በኘሮፌሰር ጋርነር /1981፡92/ ፍች መሰረት ደግሞ፡-

*"እንባ ጠባቂ ማለት የፓርላማ ተሿሚ የሆነ ግለሰብ ነው፡፡ ተግባሩም የፓርላማው ወኪል ሆኖ ስራ አስፈጻሚው በዜጎች ላይ የአስተዳደር በደሎችን እንዳይፈጽም የሚከላከል ነው፡፡"*

በመሆኑም ከላይ የተሰጡትን የእንባ ጠባቂ ፍችዎች በአንድ ላይ ጨምቀን ስናስቀምጣቸው እንባ ጠባቂ ማለት ከፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ የሕግ አውጪው አካል ተሿሚ ሲሆን እንባ ጠባቂው በሕግ እውቅና ያለው ግለሰብ (ተቋም) ነው፡፡ እንባ ጠባቂው በመንግስት አስተዳደር ሳይንስ ጥሩ እውቀት፣ ተሞክሮና ልምድ ያለው እና የመንግስት ባለስልጣናት በዜጎች ላይ የአስተዳደር ጥፋቶችን ፈጽመው ዜጎች አቤቱታዎች ሲያቀርቡለት ቅሬታዎቻቸውን መርምሮ በእነዚያ ላይ ሪፖርት የማቅረብ ስልጣን ያለው የህግ አውጪው አካል ተሿሚ ወይም የሕዝብ አገልጋይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

## *1.2 የእንባ ጠባቂ ዋና መለያ ባህሪያትና ዓለም አቀፍ ገጽታ*

### *1.2.1 የህዝብ እንባ ጠባቂ ዋና መለያ ባህሪያት*

እንባ ጠባቂ የአስተዳደር ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ የሚከላከልና ከተፈፀሙም እርምት እንዲወሰድባቸው የሚከታተል አካል ሲሆን የተለያዩ ፀሀፊዎች የሚከተሉትን የዕንባ ጠባቂ ባህሪያት አስቀምጠዋል፡፡

ዕንባ ጠባቂ፡-

1. ከመንግስት ተፅዕኖ ገለልተኛ ነው፣
2. የማያደላ መሆን አለበት፣
3. የአስተዳደር ስራዎችና የህዝብ አገልግሎቶች ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊ እና ትክክለኛ በሆነ አኳኋን የሚሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለው፣
4. ጽ/ቤቱን ለሁሉም ዜጐች ክፍት አድርጐ ማገልገል አለበት፣
5. ለሀገራዊ ደህንነት አስጊ ያልሆኑ ሚስጥራዊ ምርመራዎችን የማከናወን ችሎታ ያለውና ቅሬታ አቅራቢዎች እንዳይቀጡ የሚከላከል ነው፣
6. በመንግስት አስተዳደር የተካነ /እወቀት/ ያለው መሆን አለበት፣

7. ምርመራ የሚያከናውነው ፍ/ቤቶች ከሚከተሉት የህግ አሰራር በተለየ ነው፣
8. ለህግ አውጪው ምክር ቤት አመታዊ ሪፖርት የማቅረብ ግደታ አለበት፣

## 1.3 የእንባ ጠባቂ ተቋም ዓለም አቀፋዊ ገጽታ

የእንባ ጠባቂ ተቋም በ1809 ለመጀመሪያ ጊዜ በስዊዲን አገር እንደተቋቋመ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ዓመትም ስዊዲን አዲስ ህገ-መንግስት ያፀደቀችበት አመት የነበረ ሲሆን የእንባ ጠባቂ ተቋሙ እንደተቋቋመ የፖርላማ እንባ ጠባቂ ወይም ፖርላሜንታዊ እንባ ጠባቂ በሚል ስያሜ ይታወቅ ነበር፡፡ በ1915 የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊት የራሱ እንባ ጠበቂ የመሰረተ ሲሆን ይህ ጽ/ቤት የአገር መከላከልንና የወታደራዊ አስተዳደር ጉዳዮችን የመቆጣጠር ስልጣን ነበረው፡፡ ሆኖም በ1968 እነዚህ ሁለት የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤቶች እንዲዋሀዱ ተደርገዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ስዊዲን ውስጥ ፖርላሜንታዊ ከሆነው እንባ ጠባቂ በተጨማሪ ፖርላሜንታዊ ያልሆኑ እንባ ጠባቂዎች ይገኛሉ፡፡
ከእነዚህም ውስጥ፣

- ሌሎችን በመጉዳት ላይ ያልተመሰረተ መጠቃቀምን ለማስፈን የተቋቋመ እንባ ጠባቂ፣
- የህፃናት እንባ ጠባቂ፣
- የዘር መድልዎን የሚዋጋ እንባ ጠባቂ፣
- የፕሬስ እንባ ጠባቂ፣
- የሸማቾች እንባ ጠበቂ ወዘተ በመባል ይጠቀሳሉ፡፡

የስዊዲንን ፈለግ በመከተል ሌሎች አገሮችም የእንባ ጠባቂ ተቋም ያቋቋሙ ሲሆን ፊላንድ በ1919፣ ዴንማርክ በ1955፣ ኒውዝላንድ በ1961፣ እና ኖርዌይ በ1963 የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤቶችን አቋቁመዋል (The Free Encyclopaedia, 2006) ፡፡

አውስትራሊያ የእንባ ጠባቂ ተቋም በ1973 የመሰረተች ሲሆን ሲሪላንካ በ1981፣ ህንድ በ1962 የእንባ ጠባቂ ተቋም በመመሥረት የሚጠቀሱ አገሮች ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ፖርላሜንታዊ የእንባ ጠባቂ ተቋም ያላቸው አገሮች ብዛት 46 ናቸው፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የዕንባ ጠባቂ ታሪካዊ መሠረቱ ከስዊዲን ሲሆን የመጀመሪያው ተቋም የተመሠረተውም በዜጎች ላይ አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይደርሱና የአስተዳደር በደሎች ሲፈፀሙም ለማረም ሲሆን በተለያዩ የዓለም አገራት አስተዳደራዊ ፍትህን ለማግኘት ዜጐች እና ተቋሙ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው የዘርፉ ባለሙያዎች አስመርውበታል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ሲዊድን ውስጥ እስረኞች ተገቢነት ባላቸው ባለስልጣናት በኩል ቅሬታቸውን የመላክ መብት ያላቸው ሲሆን ማንኛውም ዜጋ የህግ ምክር ሳያገኝ ቅሬታዎቹን በቀጥታ ለዕንባ ጠባቂው ሊያሠማ የሚችል ሲሆን፣
- ፊላንድ ውስጥ ዜጐች በእንባ ጠባቂ ጽ/ቤት በመገኘት አቤቱታቸውን በቃል ሊያሰሙ ወይም በጽሁፍ ሊያቀርቡ የሚችሉ ሲሆን በፈረንሳይ ደግሞ አንድ ባለቅሬታ ቅሬታውን ይዞ በቀጥታ ወደ እንባ ጠባቂ የማይሄድ ሲሆን የፖርላማው አባል ቅሬታውን ከሰማ በኂላ ጉደዩን ዕንባ ጠባቂው እንዲከታተለው የሚያስፈልግ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይወስናል፡፡ /ድራግኒች 1981፡360/

በሌላ በኩል የዕንባ ጠባቂ የመመርመር የስልጣን ገደብ ከአገር ወደ አገር ይለያያል፡፡ በዚሁ መሠረት የስዊዲን እንባ ጠባቂ የአገሪቱን ፍ/ቤቶችና ሲቪል አገልጋዮችን አሠራር የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው ሲሆን የዴንማርክ እንባ ጠባቂ ደግሞ የማዕከላዊ የመንግስት አስተዳደሩንና በመዋቅር ሥር ያሉትን የክልል መስተዳድሮች እንዲቆጣጠርና እንዲመረምር ስልጣን ሲሰጠው የማዘጋጃቤት ጉዳዮችንና ሀይማኖታዊ ጥያቄዎችን የማየት ስልጣን የለውም፡፡ /ቻናማን 1966፡256-57/፡፡ የዴንማርክ ዕንባ ጠባቂ የአስተዳደር በደል፣ በአሠራር ላይ የጥንቃቄ ጉድለት ወይም ቸልተኝነት፣ ወይም እምነት የማጉደል ጥፋት የፈፀሙ የመንግስት ባለስልጣናት ላይ የሚቀርቡትን ቅሬታዎች የመመርመር ኃላፊነት ሲኖረው ይህን ለማድረግ ሁሉንም ኦፊሴላዊ ሰነዶችንና ቃለ-ጉባዔዎችን የማግኘት መብት አለው፡፡ በአጠቃላይ ዕንባ ጠባቂ በዜጐች ላይ የሚደርሰን የአስተዳደር ጥፋቶች በመመርመር የመፍትሔ ሀሣብ በመስጠት ሚዛናዊ የሆነ የፍትህ ስርዓት እንዲሠፍን አልሞ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ዕንባ ጠባቂ ምንም

እንኳን ከፍተኛ ተሰሚነት ሥልጣን እና ኃላፊነት ያለው የህዝብ አገልጋይ ቢሆንም የአስተዳደር ጥፋቶችን በመመርመር የመፍትሔ ሀሣብ ከመስጠት ውጪ በእነሱ ላይ ብይን ለመስጠት የሚያስችል ህጋዊ ሥልጣን የሰጡ አገሮች እንደሌሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## *1.4 የእንባ ጠባቂ ተቋም ምስረታ በተለያዩ አገሮች*

| *ተ.ቁ* | *አገር* | *ተቋሙ የተመሰረተበት ዓመት* |
|---|---|---|
| 1 | ስዊድን | 1809 |
| 2 | ታንዛንያ | 1966 |
| 3 | ፊንላንድ | 1919 |
| 4 | ጉያና | 1967 |
| 5 | ዴንማርክ | 1955 |
| 6 | ሞሪሸየስ | 1963 |
| 7 | ኖርዌይ | 1963 |
| 8 | ህንድ | 1962 |
| 9 | ኒውዝላንድ | 1971 |
| 10 | ስሪላንካ | 1981 |
| 11 | ካናዳ | 1967 |
| 12 | ፊጂ | 1972 |
| 13 | ብሪታኒያ | 1967 |
| 14 | ዛምቢያ | 1973 |
| 15 | አሜሪካ | 1967 |
| 16 | ናይጀሪያ | 1975 |
| 17 | አውስትራሊያ | 1971 |
| 18 | ኔፖል | 1990 |
| 19 | ፈረንሳይ | 1973 |

(ምንጭ፣ The Free Encyclopaedia: 2006)

## *1.5 የእንባ ጠባቂ ተቋም በተለያዩ አገሮች ያላቸው ስያሜዎች*

- Commission on Gender Equality (South African )
- Commission on Human Rights and Good Governance (Tanzania)
- Defensor del pueblo (public Defender/Ombudsman-Bolivia
- The state comptroller of Israel (Israel)
- Attorney General of the public (Italy)
- Polish Ombudsman (Poland)
- People's Advocate (Romania)
- People's Defender (Spain)
- Defensora del pueblo (public Defender/Ombudsman-Peru
- European Ombudsman
- Human rights Ombudsman ( Peru)
- Office of the Ombudsman (Namibia)
- Office of the public protector of the public of south of Africa
- Ombudsman-Botswana
- Ontario Human Rights Commission
- Ombudsman Ontario (Canada)
- Provedoria de Justicia (Portugal)
- Rwanda Ombudsman office
- Protecteur du Citoyen (Quebec-Canada)

(ምንጭ፣ EIO Five year strategic plan, The Free Encyclopaedia)

**ኢትዮጵያ በ1992 የእንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ያወጣች ሲሆን የእንባ ጠባቂ ጽ/ቤትን ደግሞ በ1997 ዓ.ም. አቋቁማለች፡፡**

# 2. የኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

## 2.1 የኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋም ለምን አስፈለገ?

በኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቂቋሚያ አዋጅ ቁጥር 211/1992 መሰረት፡-

- የኢትዮጵያ ህዝብ ለፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት እንዲሁም ለህግ ልዕልና ባካሄደው ረጅም ትግል የከፈለው መስዋዕትነት በዜጐች ላይ በዘፈቀደ የሚፈፀሙ የአስተዳዳር በደሎች የሚቀጩበትን ወይም የሚታረሙበትን ቀልጣፋ አሰራር በመዘጋት ለሰናይ መስተዳድር መሰረት የመጣልን ወቅታዊ እርምጃ የሚጠይቅ በመሆኑ፣
- የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከዜጐች የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያላቸዉ ቁርኝትና ከመብታቸው ጋር በተሳሰረ ሁኔታ የሚኖራቸው የወሳኝነት ስልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየሰፋ በመምጣቱ፣
- በዚህ ሂደት የመንግስት አስፈፃሚ አካላትና ባለስልጣኖቻቸው የሚሰጧቸውን ፍትሀዊነት የጐደላቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ ማረም ወይም እንዳይደርሱ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣
- አስተተዳደራዊ ጥፋት የተፈፀመባቸው ዜጐች ተጐድተው እንዳይቀሩ በቀላሉ ቅሬታቸውን የሚያሰሙበትና መፍትሄ የሚሹበት ተቋም የማግኘት ፍላጐታቸው መሟላት ያለበት በመሆኑ፣
- ህግ አውጪው በህዝብ ተወካይነቱ ህግ አስፈፃሚው አካል ተግባሩን በህግ መሰረት የሚያከናውንና የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የዜጐችን መብቶች የማይጋፋ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣
- ይህንኑ መርህ ለማጐልበትና ስለ ህግ አውጪው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ በመሆን ከሚያገለግሉት ተቋሞች መካከል አንዱ የሆነውን የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋም፣ ስልጣኑንና ተግባሩን በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 55/1 እና 15 መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ስልጣኑና ተግባሩ ተወስኖለት በአዋጅ ቁጥር 211/92 ተቋቁሟል፡፡

## 2.2 የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዓላማ ምንድን ነው?

የተቋሙ ዓላማ በህግ የተደነገጉ የዜጐች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ፣ የህግ የበላይነትን መሰረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡

### *2.3 የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት ምን ምን ናቸው?*

ተቋሙ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፣

- አስፈፃፀሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና አሰራሮቻቸው የዜጐችን ህገ-መንግስታዊ መብቶችና ህጐችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፣
- አስተደደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የመመርመር፣
- አስፈፃሚው አካል ስራውን በህግ መሰረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ፣
- አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ያመነበት ከሆነ የመፍትሄ ሀሳብ የመሻት፣
- አስተዳደራዊ ጥፋቶች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የማጥናትና ሀሳብ የማቅረብ፣
- የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ህጐች ወይም አሰራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ አዳዲስ ህጐች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ፣
- ከዓላማው ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

በአጠቃላይ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ መከላከልና ተፈፅመው ሲገኙም የሚታረሙበትን /የሚሻሻሉበትን/ የመፍትሄ ሀሳብ የማቅረብ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## *2.4 የኢፌዴሪ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የማያስተናግዳቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?*

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፡-

- በማንኛውም ፍ/ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን፣
- በፌደራልም ሆነ በክልል ምክር ቤቶች የተላለፈ ውሳኔና በዋና ኦዲተር በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን፣
- በፀጥታ ኃይሎችና በመከላከያ ሰራዊት ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሰኔዎችን፣
- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሀይማኖት ተቋማት ከግለሰቦችና ከውጭ ድርጅቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አያይም፡፡

## *2.5 የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ተግባራት ከሌሎች የዲሞክራሲ ግንባታ ተቋማት (ፍ/ቤቶች፣ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር ያለው ልዩነት)*

### *2.5.1 ከፍ/ቤቶች ተግባራት ጋር ያላቸው ልዩነት፣*

የተቋሙ ዋና ዋና ተግባራት ከፍ/ቤቶች ጋር ያላቸው ልዩነት፣

- ፍርድ ቤቶች በአጠቃላይ ፍትህና ፍርድ ሰጭ ሙሉ የዳኝነት አካላት ሲሆኑ ተቋሙ ግን በአስተዳደር ፍትህ ላይ የሚያተኩር ሆኖ ፍትህና ፍርድ የሚሰጠውም በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡

የአስተዳደር በደል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊፈፀም ይችላል፡፡

  - ህግን ያልተከተለ ወይም ከህግ ተቃራኒ የሆነ ውሳኔ፣
  - ውሳኔ ሳይሰጡ መዘግየት፣
  - ምክንያት አልባ ውሳኔ፣
  - ከስልጣን በላይ መጠቀም፣
  - በህግ ወይም በፍሬ-ነገር ስህተት መሰረት የተሰጠ ውሳኔና ወይም
  - እርምጃ አለመውሰድ፣
  - መረጃ አለመስጠት፣
  - ምላሽ አለመስጠትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- የፍ/ቤቶችንና የዳኞችን ህገ-መንግስታዊ ነፃነትና ገለልተኝነት ለማክበር ሲባል የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በፍ/ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን አያይም፡፡

ይህ ማለት ግን አስተዳደር ነክ የሆኑ የፍ/ቤቶች ጉዳዮችን ተቋሙ አይመለከታቸውም ማለት አይደለም፡፡

- አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ሲያምንና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዲሻሻሉ ተቋሙ በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ማድረግ የሚችል ሲሆን ይህ ለተቋሙ የተሰጠውና አንድን ጉዳይ በራሱ ተነሳሽነት ለመመርመር መቻሉ ለፍ/ቤቶች ያልተሰጠ የተቋሙ መለያ ባህሪ ነው፡፡ፍ/ቤቶች በቀረበላቸው ጉዳይ ጭብጥና ፍሬ ነገር እንጂ ራሳቸው በአወጡዋቸው ጭብጦች ላይ ምርመራ በመካሄድ መወሰን አይችሉም፡፡
- የተቋሙ የአቤቱታ አቀራረብ ስነስርዓት ከመደበኛ ፍ/ቤት የተለየ ነው፡፡ የፍ/ቤቶች ክርክር ስነ-ስርዓት ከፍተኛ ወጪና ብዙ ድካም የሚጠይቅና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ከመሆኑም ሌላ ፍ/ቤቶች በቀረቡላቸው ፍሬነገሮች ላይ ብቻ አተኩረው የሚወስኑ በመሆናቸው ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ማቅረብን የግድ የሚል፣ የባለሙያ እገዛ የሚያስፈልገው ሲሆን እነዚህ በሙሉ በእንባ ጠባቂ ተቋም የአቤቱታ ማስተናገድ ስርዓት አስገዳጅ አይደሉም፡፡የእንባ ጠባቂ የአቤቱታ አቀራረብና ማስተናገድ ስርዓት የባለሙያ እገዛ የማያስፈልገው፣ ወጪ የሌለው እና ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የሌለው ነው፡፡
- በፍ/ቤቶች ህግ ስነ-ስርዓት አቤቱታ ለማቅረብ ልዩ ጥቅም መነካቱን ማሳየት ግዴታ ነው፡፡ አንድ ሰው በህግ የተከበረ ጥቅሙ ካልተነካ ለፍ/ቤት አቤቱታ ለማቅረብ በቂ ምክንያት ላይኖረው ይችላል፡፡ ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ግን ሶስተኛ ወገን ወይም ማህበር አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡ ስለሆነም የተቋሙ ባህሪ ከአቤት ባይ ማንነት ይልቅ በጉዳዩ ምንነት ላይ የሚያተኩር መሆኑ ተቋሙን ከፍ/ቤቶች ሲለየው በፍ/ቤቶች ለአንድ ጉዳይ መታየት የጉዳዩ አቅራቢ ማንነት ወሳኝነት አለው፡፡
- የእንባ ጠባቂ ለአቤት ባዮች የተለየ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን አሰራሩና መመሪያቹ በሙሉ ፍትህ ላጣ አቤት ባይ ወገንተኛ ሆነው የተቀረፁ ናቸው፡፡
- የሕዝብ እንባ ጠባቂ የአቤቱታ አቀራረብ ስነስርዓት ቀላል ከመሆኑም ሌላ አቤቱታዎች በቃል፣ በጽሑፍ፣ በስልክ፣ በኢ-ሜይልና በሌሎችም መንገዶች ሊቀርቡ የሚችሉ ሲሆኑ ቋንቋ ባለመቻል ሰበብ አቤት ባዮች ላይ ችግር እንዳይፈጠር አቤት ባዩ በሚፈልገው ቋንቋ አቤቱታውን ሊያቀርብ

እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እንደአቤቱታው ክብደት አቤት ባዩ ማንነቱን ሳያሳውቅ አቤቱታውን ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይህም ግለሰቦች የመንግስት ሹማምንትን በመፍራት አቤቱታ ከማቅረብ እንዳይገቱ ለማድረግ የህግ ከላላ ለመስጠት ነው፡፡

- ሌላው የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋነኛ ስራና ለፍ/ቤቶች ያልተሰጠ ስልጣን ቁጥጥርና ክትትል የማድረግ ተግባር ነው፡፡ ይህ ተግባር ማንኛውንም አቤቱታ ከመፍታት አነንፃር ብቻ ሳይሆን የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ህጐች ወይም አሰራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ህጐች እንንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ ለመንግስት የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ማሳመንና በተግባር ላይ እንዲውሉ ማድረግን የሚያጠቃልል ተግባር ነው፡፡ ተቋሙ የመንግስት አካላት ስራቸውን በህገ-መንግስቱና በህግ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት ስለመከናውናቸው ቁጥጥር የሚያደርግ በመሆኑ አገልግሎት ሰጪ የመንግስት ተቋሞች ለተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚሰጧቸውን የአገልግሎት ሁኔታዎች ክትትልና ግምገማ የሚያደርግ ሲሆን በክትትልና ግምገማዎች የሚገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ችግር የተስተዋለባቸው አሰራሮች እንዲለወጡ መንግስትን ማማከርና የለውጥ ሀሳቦች የሚያቀርብ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ግን የዚህ ዓይነት ተግባር አያከናውኑም፡፡

- ከተቋሙ ዋና ዋና ተግባሮች አንዱ ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት ማድረግና በመገናኛ ብዙሀን የምርመራ ግኝቱንና ሌሎችንም አስፈላጊ ጉዳዮች ለሕዝብ በይፋ ማሳወቅ ነው፡፡ ይህ የተቋሙ ተግባር የአስተዳደር በደል ለሚያደርሱ፣ የዜጐችን ሰብዓዊ መብት ለሚጥሱና መልካም አስተዳደርን ለሚያጓድሉ የመንግስት አካላትና ባለስልጣናት "ውርደት ማከናነብ" ሊባል የሚችል የተቋሙ ዋነኛ ተግባር ሲሆን ይህ ተግባር አንድ የመንግስት አካል የተሰጠውን ማሳሰቢያ በተገቢው አኳኋንና ጊዜ ሳይፈጽም ቢቀር ተቋሙ የሚጠቀምበት ስልጣኑ ነው፡፡

በአጠቃላይ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ለአስተዳደር ፍትህ መስፈን ጥናትና ምርምር በማከናወን፣ በማስተማር፣ በዜጐች ላይ በዘፈቀደ የሚፈፀሙ

የአስተዳደር በደሎች የሚቀጩበትን ወይም የሚታረሙበትን አሰራሮች እንዲቀየሱ የማሳሰብ ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን ተቋሙ ፍ/ቤቶችን የሚተካ ሳይሆን አማራጭ የጥፋትና ስህተት ማረሚያ መስመሮችን በመዘርጋት የፍ/ቤቶችንና ሌሎች የዳኝነት አካላት አጋዥ ሆኖ የሚያገለግል ተቋም ነው፡፡

## *2.5.2 ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን*

የኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ጋር ያለውን የተግባር ልዩነት ለመረዳት ከዚህ በላይ የቀረበውን የተቋሙን ዓላማና ተግባር ቀጥሎ በቀረበው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር ጋር ማገናዘቡ በቂ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዓላማ፡-

- ህዝቡ ስለ ሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣ መብቶቹ እንዳይጣሱ መጠበቅ፣ መብቶች ሳይሸራረፉ ስራ ላይ እንዲውሉና ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ሲሆን የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

## *ስልጣንና ተግባር*

- በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ውስጥ የተደነገጉት ሰብዓዊ መብቶች በማንኛውም ዜጋ፣ በመንግስት አካላት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች በሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው መከበራቸውን ማረጋገጥ፣
- በመንግስት የሚወጡ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም ትዕዛዞች በህገ-መንግስቱ ከተረጋገጡ የዜጐች ሰብዓዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- ህብረተሰቡ ስለ ሰብዓዊ መብት በቂ ዕውቀት ኖሮት መብቱን የማክበርና የማስከበር ባህል እንዲያዳብር በመገናኛ ብዙሀንና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር፣
- የሰብዓዊ መብት መጣስ ቅሬታዎች ሲቀርቡለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ምርመራ ማድረግ

- በሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት፡፡

ከላይ እንደሚታየው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ዋና ዋና ተግባራት በአብዛኛው የሚያተኩሩት በሰብዓዊ መብቶች መከበር ዙሪያ ሲሆን የህዝብ እንባ ጠባቂ ተግባር የሚያተኩረው በመንግስት አስተዳደር በደል ዙሪያ መሆኑ የሚለያቸው ቢሆንም ተቋሙና ኮሚሽኑ በዲሞክራሲ ግንባታ ያላቸው ሚና ሊያመሳስላቸው ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ከፌደራሉ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ የሚከተለውን የሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች ማስተዋሉ ተገቢ ይሆናል፡፡

## *2.5.3 ከስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች*

### *የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዓላማዎች*

- የስነ-መግባርና የፀረ-ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የነቃና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ህብረተሰብ እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣
- የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን መከላከል፣
- የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሰራርን በማጋለጥ፣ በመመርመርና በመክሰስ በአገሪቱ ውስጥ ሀቀኛ የህዝብ አገልግሎት እንዲሰፍን ጥረት ማድረግ፣
- ለመንግስት ባለስልጣኖች እና ለመንግስት ሠራተኞች የሚያገለግሉ የስነ-መግባር ደንቦች እንዲያዘጋጁ ማድረግ፣ ተፈፃሚነታቸውን መከታተልና ሌሎች ለሚያዘጋጁቸው የስነ ምግባር ደንቦች ሲጠየቅ ድጋፍ ማድረግ፡፡

# ክፍል ሦስት

## 3. መልካም አስተዳደር ምንድን ነው?

በፅንሰ ሀሳብ አኳያ አስተዳደር የሚለው ቃል አዲስ የተፈጠረ ሳይሆን ከሰው ልጅ ስልጣኔ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ ቃል በግርድፍ ፍቺው አንድ አገር /ተቋም/ በማስተዳደር ረገድ የሚሰጡ ውሳኔዎችንና አፈፃፀማቸውን የሚያካትት ሲሆን አንዳንዶቹ “መልካም” ወይም ሰናይ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አይደሉም፡፡ መልካም የሆነውን አስተዳደር መልካም ካልሆነው ለመለየት ሲባል መልካም አስተዳደር የሚለው ሀረግ እንደተፈጠረ የተለያዩ ፅሁፎች ያመልክታሉ፡፡

በዚህ መሰረት በርካታ የልማት አጋሮችና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና መልካም ያልሆነውን ለመቀነስና ለማጥፋት የተለያዩ ስልቶችን ቀይሰው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ እንቅስቃሴያቸውን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃርም መልካም አስተዳደርን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የለውጥ እርምጃ መውሰድን ለሚሰጡት የልማት ዕርዳታና ብድር ቅድመ-ሁኔታ ማድረጋቸው ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡

## 3.1. የመልካም አስተዳደር መገለጫ ባህሪያት

ሁለቱ የገንዘብ ተቋማት የውጭ ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ፍላጐትና የህዝብ ሀብት ለታቀደለት አላማ መዋሉን ከማረጋገጥ አኳያ ከአምስት የማይበልጡ የመልካም አስተዳደር ባህርያት ነበሩት:: እነሱም በህግ የሚገዛ፣ ቀልጣፋ፣ ከሙስና የፀዳ፣ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራርን መዘርጋት ነበር፡፡

በአፍሪካ አህጉር መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች ላይ በተካሄደ ጥናት የመልካም አስተዳደር ዋና ዋና ባህርያት አራት ናቸው፡፡ እነሱም የስልጣን /የፖለቲካ/ ውክልና፣የኢኮኖሚ አስተዳደር፣ የተቋማት ውጤታማና ተጠያቂነት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የአለም ባንክ እ.ኤ.አ. መስከረም 2006 ባወጣው የጥናት ማጠቃለያ የመልካም አስተዳደር መገለጫዎችን በስድስት መድቧቸዋል እነሱም፡-

1. የህዝብ ተሳትፎና የመንግሥት ተጠያቂነት፤
2. የፖለቲካ መረጋጋትና ብጥብጥ አለመኖር፤
3. የመንግሥት ውጤታማነት /አገልግሎት በመስጠት ረገድ/
4. የመንግሥት የቁጥጥር ሥርዓት ጥራት /የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ውጤታማ ሆኖ መሠራት እንዲያስችለው/
5. የሕግ የበላይነት
6. ሙስናን መከላከል /መቆጣጠር/ ናቸው፡፡

ስለ መልካም አስተደደር መገለጫ ስናስብ አስተዳደርን በተመለከተ ማንኛውም መልካም የሆነ ነገር ሁሉ የመልካም አስተዳደር መገለጫ መሆኑን ባለሙያዎች ይስማሙበታል፡፡ በመልካም አስተዳደር ተዘውትረው የሚጠቀሱ ስምንት የመገለጫ ባህሪያት የሚከተሉት ናቸው ፡፡ እነሱም፡-

*1. አሳታፊነት*

አሳታፊነት ማለት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በውሳኔ አሰጣጥ የሚሳተፉበትና በልማት ዕቅዶች ላይ በባለቤትነት የሚንቀሳቀሱበት ስርዓት ማለት ነው፡፡ ዜጐች በመንግስት ፖሊሲ አወጣጥና አተገባበር እንዲሁም ውሳኔ የዜጐች ተሳትፎ እንዲጐለብት ባልተማከለ አስተደደር ሥልጣን ወደታችኛው የአስተዳደር ክፍል ለምሳሌ ወደ ወረዳና ቀበሌ ይወርዳል፡፡

*2. በህግ የበላይነት መመራት*

መልካም አስተዳደር ዜጐችን በዘር፣ በሀይማኖት እና በፖለቲካ አመላካከት ወዘተ ሳይለይ በዕኩልነት የሚያይ የፍትህ ስርዓት ያስፈልገዋል፡፡ የህግ የበላይነት ፍትሀዊ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ኖሮት ህጎች ያለአድልዎ የሚተገበሩበትና ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች መብት የሚከበርበት ስርዓት ነው፡፡ የህግ የበላይነት ማለት ዜጐች ህጉን እንዴት እንደሚረዱት፣ እንደሚያከብሩትና እንደሚገለገሉበት ያላቸውን ግንዛቤ የሚጨምር ሲሆን በመንግስት አሰራርም ላይ ተጠያቂነትን ያዳብራል፡፡

*3. ተጠያቂነት*

ተጠያቂነት ለመልካም አስተዳደር መስፈን ቁልፍና ተፈላጊ ጉዳይ ሲሆን የመንግስት ተቋማት/ባለስልጣናት/፣ ኃላፊዎች በሚሰጡት አገልግሎት ለሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ለሚወስዷቸው እርምጃዎች ለባለድርሻዎችና ለህብረተሰቡ ተጠያቂ መሆን ይገባቸዋል፡፡ አንድ ድርጅት/ተቋም/ ለሚወስደው እርምጃና ለሚሰጣቸው ውሳኔዎች ሀላፊነቱን መውሰድ፣ ጥያቄ ለሚያነሱ ወገኖች ደግሞ መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡ የመንግስት ተጠያቂነት መንግስትን እንደ ባለሥልጣን የሚመለከት በመሆኑ ሃላፊዎች ለሚሰጡት ውሣኔና ለሚወስዱት እርምጃ በህግ መሠረት ተጠያቂዎች ናቸው፡፡ ተጠያቂነት ሙስናን ለመዋጋት አይነተኛ መንገድ ሲሆን ውጤቱም በህግ የበላይነት መርህ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

*4. ግልፅነት*

*ግልፅነት ህጐችን፣ ደንቦችን/መመሪያዎችን/ በመከተል ውሳኔዎችን መወሰንና አርምጃዎችን መውሰድን የሚያካትት ሲሆን፤ የሚሰጡ ውሳኔዎችና የሚወሰዱ እርምጃዎችን ዜጐች እንዲያውቋቸው በቀላሉና በበቂ ሁኔታ መረጃ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ግልጽነት የመንግስት ውሳኔ አሰጣጥና አተገባበር ግልጽ ሆኖ የገንዘብ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትና ተቆጣጠሪ መሥሪያ ቤቶች አስፈላጊውን መረጃ ለህዝብ እንዲሰጡ የሚያስገድዳቸው ህግ እንዲኖር ይጠይቃል፡፡*

5. *ርዕትን የተከተለና ሁሉን የሚያቅፍ መሆን*

መልካም አስተዳደር ለጥቂቶች ሳይሆን ለሁሉም ዜጐች አስፈላጊ በመሆኑ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች /ሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞችን/ በፖሊሲ ቀረፃና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ በባለቤትነት ስሜት እንዲሳተፉ ማድረግ አለበት፡፡ ቀድሞ የነበሩ ኢ-ፍትሀዊ ሁኔታዎችን ለማስወገድና እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች እኩል

ተጠቃሚ ለማድረግ አንዳንድ የማካካሻ ሁኔታዎችን ማመቻቸትንም ይጨምራል፡ በዚህም ሁኔታ ርትዕ ወደ እኩልነት ያመራል፡፡

## 6. ለህዝብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ መስጠት

መልካም አስተዳደር ሊሰፍን የሚችለው ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ በተገቢው ጊዜ ሊሰጥ የሚችል ተቋም ሲገነባ በመሆኑ የመንግስት ተቋማት የተልጋዩን ህብረተሰብ አስተያየት፣ ጥያቄና ፍላጐት ለማሟላት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም የመንግስት አስተደደር ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያገለግል መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ህብረተሰቡ በየደረጃው የሚያጋጥመውን ችግር ለመፍታት አስፈላጊውን ምላሽ በወቅቱ ለመስጠት መንግስት በቁርጠኝነት መንቀሳቀስ አለበት፡፡

## 7. ውጤታማነት

በእጅ ያለ መዋዕለ-ንዋይን በአግባቡ በመጠቀም የተገልጋዩን ህብረተሰብ ፍላጐት ለማሟላት ውጤታማ የስራ አገልግሎት መስጠት ከመልካም አስተዳደር መገለጫዎች አንዱ ሲሆን የመንግስት ተቋማት የህዝቡን ፍላጐት በየደረጃው ለማርካት የሚችል ዘላቂነት ያለው ውጤታማ ስራ መስራት አለባቸው፡፡ በዚህ መሠረት የመንግስት አካላት ያለውን ውስን የተፈጥሮ ሀብት ቆጥቦ በመጠቀምና አካባቢን በመጠበቅ ውጤት ማስመዝገብ አለባቸው፡፡

## 8. የጋራ መግባባት

በአንድ አገር ውስጥ የተለያዩ ህዝቦች እንደመኖራቸው መጠን የፍላጐቶችም ልዩነት በዚያው መጠን የሰፋ ነው፡፡ መንግስት በሚሰጠው አገልግሎት በሙሉ እነኝህን የተለያዩ ፍላጐቶች በማስታረቅ እያንዳንዱ ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚሆንበትን አቅጣጫ መሻት አለበት፡፡ ይህንን ለማድረግም የሁሉንም ህዝቦች ታሪክና ባህል ያገናዘበ ሰፊ የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ያስፈልገዋል፡፡ ዜጐች በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ መግባባት ላይ መድረስ ይኖርባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ በአንድ አገር ላይ እንከን የለሽ መልካም አስተዳደርን ሙሉ በሙሉ እውን ለማድረግ ቢያስቸግርም በጣም የተወሰኑ አገሮች ከምንም በላይ አስፈላጊ የሆነውን መልካም አስተዳደርን በአገራቸው ለማስፈን በመቃረብ ላይ ይገኛሉ። ዘላቂነት ያለው የህብረተሰብ ዕድገት እንዲኖር ካስፈለገ መልካም አስተዳደርን ዕውን ሊያደርጉ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በመውሠድና በመተግበር አንጻር ሁሉም የህብረተሰቡ አካላት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የማይተካ ሚናውን መጫወት ይኖርበታል።

### *3.2 መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚያስፈልጉ የፖሊሲ ድጋፎች*

የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በዜጎች ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የመልካም አስተዳደር መስፈን የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። መልካም አስተደደርን ለማስፈን በህገመንግስት የተመሠረተውን የዲሞክራሲያ ሥርዓት ለመጠበቅና ለማሻሻል በዋናነት በህገመንግስት መርሆዎችና እሴቶች የሚያምን መብቱን የሚያስከብርና የሌሎችን መብት የሚያከብር እንዲሁም ብልሹ አሰራርን በቁርጠኝነት የሚዋጋ ዜጋ ለመፍጠር የፖሊሲ ድጋፎች ያስፈልጋሉ ። ይህንን ዓላማ ማሳካት የሚቻለው ፈጻሚና አስፈጻሚ አካላት፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሲቪል ማህበራት፣ የሙያና የብዙሃን ማህበራት በጋራ ያላሰለሰ ተሳትፎ ሲያደርጉ ነው።

ከዚህ አኳያ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ተፈላጊ የሚሆነው የፖሊሲ አቅጣጫ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

- የዳኝነት ሥርዓቱ ህዝቡ ያፀደቀውን ህገመንግስት በትክክል በመተርጐም ለባለጉዳዩ ፈጣን፣ ትክክለኛ ያለአንዳች አድልዎ ፍትህ መስጠት፣
- ስራ አስፈጻማው አካል በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ተወካዮች ያፀደቋቸውን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በተሟላ ሁኔታ በመፈጸም ለሁሉም ዜጋ ፈጣን አገልግሎት መስጠት፣
- ለመንግስት ሥራ የተመደበላቸውን ገንዘብ በአግባቡና በቁጠባ ለታቀደለት ዓላማ ማዋል፣

- አድልዎ የሌለበት መንግስታዊ አገልግሎት ለመስጠት ፍትሃዊ የሆነ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት፣
- የልማት አጀንዳዎችን ለማሳካት የዜጎችን መብትና እኩልነት ለማረጋገጥ የአስፈጻሚው አካል አቅም መገንባት፣
- ዜጐች በፈለጉት የኢኮኖሚ ዘርፍ ተንቀሳቅሰው እንዲሠሩ ማስቻል:: አምራችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ :: ለዚህም ጉዳይ የመንግስት ፖሊሲ ህግና አሠራር አስፈላጊ ነው፡፡

ከላይ ለማመልከት የተሞከረው የፖሊሲ አቅጣጫ በአሁኑ ጊዜ ዲሞክራሲ ሥርዓትን በሚያራምዱ ሀገራት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል፡፡ ግሎባላይዜሽን የዓለም እውነታ በሆነበት ሙስናና ብልሹ አሠራር የእድገት ጠንቅ በሆኑበት በዚህ ጊዜ የህግ የበላይነትን ማረጋገጥ የሚቻለው የመልካም አስተደደርን ባህል እንደመግባቢያ ቋንቋ ዘወትር መነጋገር ሲቻል ነው፡፡ መልካም አስተዳደር በማንኛውም የዲሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ የቆየና አሁንም ያለ የጥሩ ሥርዓት መገለጫ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የመገናኛ ብዙሃን እጅግ በረቀቀበት በዚህም የተነሳ ዓለም ወደ ትንሽ መንደር በተለወጠችበት የግሎባላይዜሽን ዘመን ለመልካም አስተዳደር መስፈን የሚያፈልጉ የፖሊሲ ድጋፎች ከጊዜው ጋር አብረው መራመድ አለባቸው :: በዚህ መሰረት መልካም አስተዳደር ለማስፈን የሚከተሉትን ነጥቦች ማጤን ያሻል::

- የመንግስት አሰራር ቀልጣፋና ጥራት ያለው ሆኖ ዜጐችን የማያንጋላታና ስራቸውን የማያንጓትት ሲሆን ፡ ቀልጣፋና ጥራት ያለው የመንግስት አሰራር ሊገኝ የሚችለው ደግሞ የተለያዩ ሀሳቦች ከየትም መንጭተው ሲመጡና አማርጦ መውሰድና መጠቀም ሲቻል ነው፡፡ የተለያዩ ሀሳቦች መንጭተው ሲመጡ መውሰድና መጠቀም የሚቻለው ደግሞ መብቶች ሁሉ የተከበሩበት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሲኖር ብቻ ነው፡፡
- ከሙስናና ከአድልዎ የፀዳ መንግስት ከሌለ መልካም አስተዳደር ማግኘት አይታሰብም፡፡ ሙስናና አድልዎ እንደ ስርዓት የማይቀጥልባት ነገር ግን አልፎ አልፎ ሊያጋጥም የሚችል ለስርዓቱ አደጋ የማይሆን መንግስት ሊኖር ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት ባለስልጣናትና

ሰራተኞች ለመልካም ስራቸው የሚመሰገኑበትና የሚሸለሙበት እንዲሁም ለሙስናና አድልዎ የሚጠየቁበት አሰራር ሲኖር።

- መልካም አስተዳደር ሊሰፍን የሚችለው ሕዝቡ በየደረጃው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከልማቱ ተጠቃሚ ሲሆን ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ፍትህ መጓደልና አለመጓደሉን መረጋገጥ የሚቻልበት የደሞክራሲ ስርዓት ሲመሰረት ብቻ ነው።
- ስር የሰደደው ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ባህል በዲሞክራሲያዊ ባህል ሲተካ በምላሹ የዜጎች መብቶች ሁሉ ተከብረው ልማትና መልካም አስተዳደር ሊገኝ ይችላል። መልካም አስተዳደር ስለተፈለገ ብቻ ሊገኝ አይችልም መልካም አስተዳደር ሊገኝ የሚችለው የብልሹ አስተዳደር ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን በማስወገድ ብቻ ነው።

### 3.3 መልካም አስተዳደር ለዘለቄታዊ ልማት ያለው አስተዋጽኦ

የመልካም አስተዳደር ፅንሰ ሀሳብ በሁለቱ የዓለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማት የተገለጸው እንዳለ ሆኖ በምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ ኢሲያ ሀገሮች ቃሉ ፋሽን እየሆነ የመጣው ሀገሮች የኢኮኖሚ ድቀት ካጋጠማቸው በኋላ ነው። በአፍሪካ ሀገራትም ለሚታየው የእድገት ችግር መንስኤው የመልካም አስተዳደር አለመኖር መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል። ይኸውም ኢንቨስትመንት ሊኖር የሚችለው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት ግልጽነትና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ከሙስና ጸድተው ሃላፊነታቸውን በአግባቡ ሲወጡ ነው። የአገልግሎት መስጫ ተቋማትና መሠረተ ልማት ሊስፋፉ የሚችለው ከህዝብ የተሰበሰበው ግብር በአግባቡ ለታቀደለት ዓላማ ሲውል ብቻ ነው።

ሙስናና ብልሹ አስተዳደር የልማት መሰረታዊ ችግሮች ስለሆኑ ለሀገር እድገት እንቅፋት መሆናቸው እሙን ነው። ይህን ችግር ሊቀርፍ የሚያስችል የእድገት መንገድ የሚጠርገው ከመልካም አስተዳደር መገለጫ ባህሪያት ውስጥ በአብዛኛው ላይ ጠንከር ያለ ስራ የተሰራ እንደሆን ነው። ለምሳሌ አለም ባንክ እ.ኤ.አ. መስከረም 2006 ላይ ባወጣው ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያ

በአንዳንዶቹ የመልካም አስተዳደር መግለጫ ባህሪያት ላይ ጠንክራ ስትሰራ በሌሎች ላይ ደከም እንዳለች ነው የገለፀው፡፡ ስለዚህ መልካም አስተዳደርና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ቀጥታ ግንኙነት እንዳላቸው የሚያከራክር አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መልካም አስተዳደር ካለ ድህነትን ኋላ ቀር አስተሳሰብንና የኤች አይቪ ኤድስ ወረርሽኝን መቀነስ ይቻላል፡፡

መልካም አስተዳደር ካለ ዘለቄታዊ የሆነ ልማት አለ የምንለው የኢኮኖሚ እድገታችን ደረጃ የሚወስነው መልካም አስተዳደር በሰፈነበት መጠን ነው፡፡ መልካም አስተዳዳሩ መለስተኛ ከሆነ የልማት እንቅስቃሲያችንም መለስተኛ ደረጃ ላይ ነው የሚሆነው፡፡ እንዲሁም መልካም አስተዳደራችን ዝቅተኛ ከሆነ እድገታችንም ዝቅተኛ ነው፡፡ ነገር ግን መልካም አስተዳደር ሰፍኗል ማለት አሀኑኑ የኢኮኖሚ እድገት ውጤት መታየት አለበት ማለት አይደለም፡፡ ይኸውም በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ ለምሳሌ በትምህርትና በጤና ዘርፍ መልካም አስተዳደር መስፈን በዚህ የፖሊሲ አሰራር ለውጥ ምክንያት የተማረና ጤነኛ ዜጋ ሊኖረን የሚችለው ገና በሚቀጥሉት አስርተ ዓመታት ነው፡፡ በሌላ በኩል ንግድና ኢንቨስትመንትን በተመለከተ መልካም አስተዳደር አለ ስንል በሚቀጥለው አመት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ንግድና ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዜጐች ወይም የውጭ ባለሀብቶች አሁን ባለው በጊዜያዊ መልካም አስተዳደር መስፈን ተበረታትተው መዋለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ፡ስለዚህ ዘላቂታዊነት ያለው ልማት ለማምጣት አሁን ያለው መልካም አስተዳደር ዘለቄታዊና ወደኋላ የማይመለስ መሆኑን ማረጋገጥያስፈልጋቸዋል፡ ስለሆነም የመልካም አስተዳደር መስፈን ለዜሌቄታዊ ልማትና የሀገር እድገት ያለው ሚና ኢትዮጵያ የፈጠረችው ሳይሆን በማንኛውም የዲሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የሚኖር የኢኮኖሚ የማህበራዊ ለውጥ ሂደት መሆኑ ሊሰመርበት ይገበል፡፡

### *3.4. መልካም አስተዳደር ተሞክሮ በኢትዮጵያ*

መልካም አስተዳደር ከጥሩ የህግ ማዕቀፍ ይጀምራል፡፡ ጥሩ የህግ ማዕቀፍ መኖር የሀገሪቱን ሀብት በአግባቡ ለማስተዳደር የሚጠቅም ሲሆን ብቃት ያለው ዳኝነት ሲኖር ደግሞ የሚነሱ አለመግባባቶችን በገለልተኝነት ለመዳኘት ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት አንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እንደ ነፃ የዳኝነት አካል ማንኛውንም በፍርድ ሊወሰን የሚችል ጉዳይ ለመወሰን ተቋቁሟል፡፡ የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ መከናወን እንዳለበት ማንኛውም ሃላፊና የህዝብ ተመራጭ ሃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ እንደሚሆን አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ይደነግጋል፡፡ መንግስት ሕዝቡን ለልማት ማሳተፍና የሕዝቡንም የልማት እንቅስቃሴ መደገፍ እንዳለበት በህገ መንግስቱ ተደንግጓል፡፡

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ም/ቤቱ ባወጣቸው ህጐች መሰረት የተቋቋሙ ተቋማት አሉ፡፡ እነዚህ ተቋማትም ስለ ም/ቤቱ ሁነው የስራ አስፈፃሚውን አሰራር ለመቆጣጠር የተቋቋሙ ናቸው፡፡ እነሱም፡-

1ኛ. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም : ኃላፊነቱ አስተዳደራዊ በደልን ለማስወገድ ሲከሰቱም መፍትሔ ለማሻት፣

2ኛ. የሰብአዊ መብት ኮሚሽን: ኃላፊነቱ የሰብአዊ መብት ትምህርት ለማስፋፋት ህገ-መንግስታዊ መብቶች እንደከበሩ ማድረግና ተጥሰውም ሲገኙ የእርምት እርምጃ መሻት፣

3ኛ. የዋናው ጠቅላይ ኦደተር ጽ/ቤት : ኃላፊነቱ የፌደራሉን መንግስት መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን መቆጣጠር፣

4ኛ. የምርጫ ቦርድ: ኃላፊነቱ በፌደራልና በክልል ደረጃ ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኛነት ለማካሄድ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በአዋጅ የተቋቋሙት የአቅም ግንባታ ሚኒስቴርና የስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን መልካም አስተደደርን በማስፈን ረገድ አይነተኛ ተቋማት ናቸው፡፡ ሌሎች የመንግስት ተቋማት ለመልካም አስተዳደር መስፈን ሚና የላቸውም ማለት ሳይሆን ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተቋማት ግን

ቀጥተኛና ዋና ኀላፊነታቸው ከመልካም አስተዳደር መስፈን ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡ በአፈፃፀም ደረጃ መንግስት የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚገባው የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ሲሆን በተለይም የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ኘሮግራም፡ የመንግስት ግብር ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግራምና የፍትህ አስተዳደር ስርዓት ማሻሻያ ኘሮግግራም ለመልካም አስተዳደር መስፈን ግንባር ቀደም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ እነዚህን የማሻሻያ ኘሮግራሞች ለማሳካት የመንግስት አስፈጻሚ አካላት አስፈላጊውን ስልጠና ከመስጠት ጀምሮ ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው፡፡

እነዚህ የማሻሻያ ኘሮግራሞች በቀጥታ ያነጣጠሩት ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሳታፊና ከሙስና የፀዳ ቀልጣፋ የመንግስት አገልግሎት በመስጠት ላይ በመሆኑ በውስጣቸው የመልካም አስተዳደር እሴት እናገኛለን፡፡ የመልካም አስተዳደር ማህበራዊ እሴቶች ያለፉት ጊዜያት ችግሮቻችንን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የመልካም አስተዳደር ተሞክሮ በኢትዩጵያ የዲምክራሲ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ንቁ ተሳታፊዎችን ከማፍራት አንፃር ከፍተኛ ስፍራ ይዞ ይገኛል፡፡

### *3.4.1. መልካም አስተዳደርን በኢትዮጵያ ለማስፈን ያጋጠሙ ችግሮች*

የማንኛውንም ሀገር ልማትና እድገት ከሚወስኑት ተግባሮች አንዱ የመልካም አስተዳደር መስፈን ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ ሀገራችን መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ባደረገችው እንቅስቃሴ ሰፊና በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በአንድ አንድ መ/ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ የአገልግሎት ማሻሻል ለማምጣት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት በመልካም አስተዳደር ዙሪያ በሕዝቦች መብት መከበር ላይ ሰፋ ያለ ትምህርትና ግንዛቤ ከተሰጠ የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት አበረታች ጅምር መሆኑ በግልፅ ይታያል፡፡ ሆኖም በበርካታ መ/ቤቶች ውስጥ ችግሮች መታየታቸው አልቀረም፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-

#### *1. የግንዛቤና የትኩረት ማነስ ችግር*

ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ የሰላምና የልማት እቅዶቻችንን እውን ለማደረግ ሕዝቡን ስለመልካም አስተዳደር ግንዛቤ ማስጨበጥ ይጠበቅብናል፡፡ ሆኖም ይህንን ተግባር ቀጥታ ወደ ህዝቡ የማድረስ ጉዳይ ገና ብዙ የሚቀረን ነገር አንዳደለ በርካታ ጉደዮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የወጣው ፖሊሲና ስትራቴጂ ለማስፈፀም የሚያስችል የአቅም ውስንነት መኖሩ፡፡ የማስፈፀም አቅም ስንል በተጨባጭ ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰለጠነ በጥሩ ስነ-ምግባር የታነፀ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠንና አይነት ማፍራት ማለት ነው፡፡ መልካም አስተዳደርን በተሳካ ሁኔታ ለማስፈን ሕዝቡ በየደረጃው የልማት ተጠቃሚ እንዲሆን በሚደረገው ርብርቦሽ በአንዳንድ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች የግንዛቤ ማነስና ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠት በሰፊው ተንፀባርቋል፡፡

በመሆኑም በሁሉም ደረጃዎች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ፅንሰ ሀሳብ ወደ ሁሎም አስፈፃሚዎች ሰርፆ እስኪገባ ድረስ ብዙ ስራ ይጠይቃል፡፡ የግንዛቤ ማነስና ለጉደዩ ትኩረት አለመስጠት ያለው ችግር አሁንም በየመ/ቤቱ በፍትህ እጦት የሚንገለታው የህብረተሰብ ቁጥር ከፍተኛ ነው፡፡

## 2. የቴክኒካዊ ብቃት ችግር

መልካም አስተዳደር በየደረጃው ለማስፈን ከፍተኛ የሆነ የቴክኒክ ብቃት እንደሚያስፈልግ እሙን ነው፡፡ ሆኖም በአብዛኛው አስፈፃሚ አካላት ላይ የቴክኒክ ብቃት ችግር መኖሩ ግልፅ ነው፡፡ በአፈጻጸም ላይ በታዩ የቴክኒካዊ ብቃትና ጥራት ችግሮች ምክንያት በምንፈልገው ፍጥነት መልካም አስተዳደርን ባናሰፍንም የመልካም አስተዳዳር ባህል ማንሰራራት ተጀምሯል፡፡ በዚህም መሰረት የሚታዩትን ችግሮች በየደረጃው እየቀረፍን በመሄዳችን ላለፉት አራት አመታት ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ጉልተው የሚታዩትንና ለወደፊት ሊታዩ የሚችሉትን የመልካም አስተዳዳር ቴክነካዊ ብቃት ችግሮች በትምህርት፣ በውይይት፣ በግምገማና በአስፈፃሚው ቁርጠኝነት ማስተካከል እንደሚቻል በተግባር ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል የዲሞክራሲ ባህልን ለማጉልበት የሚመለከተው ህግ በማውጣት መንግስት ብቻ ሳይሆን በህገ መንግስቱ የተቀመጡትን እሴቶችና መርሆች ወደ ተግባር

መለወጥ የሚያስችል አቅም ሲፈጠር ብቻ ነው፡፡ ይህ አቅም የሚፈጠረውም በተከታታይ በሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

*የአመራሩ ቁርጠኝነት ማነስ*

የማስፈፀም አቅም ግንባታው ሂደት የራሱ ቴክኒካዊ ችግሮች እንደሉት ግልጽ ቢሆንም መንግስት ያወጣውን ስራትቴጂ ግብ ለማድረስ እስከ አሁን ከፍተኛ ርብርቦሽ ተደርጓል፡፡ መልካም አስተዳደርን በቁርጥኝነት ለማስፈን የሚቻለው አስፈጻሚው አካል ለለውጥ ዝግጁ መሆን ሲችል ነው፡፡ የመንግስት አመራር ከህብረተሰቡ የተገኘ ስለሆነ በውስጡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች አመለካከቶችና አዝማሚያዎች የታጠረ መሆኑ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ አስፈጻሚው አካል በዚህ ሂደት እራሱን እስካልለወጣ ድረስ መሀል ላይ እየዋለለ ፕሮግራሙን በቁርጠኝነት ሳይተገብረው ይቀራል፡፡ ከውስጡ ያሉትን የተሳሳቱ አመለካከቶች አውጥቶ መልካም አስተዳደርን ከልማትና ከሀገር ዕድገት ጋር አቆራኝቶ ሌት ተቀን ተረባርቦ ከመፈፀም ይልቅ ሥራው ወደፊት እየተንከባለለ ይታያል፡፡ በአስፈጻሚው አካል የሚታየው ችግር በዋነኛነትለውጥን ከማይቀበሉ ኋላቀር አስተሳሰቦች ጋር መቆራረጥ አለመቻል ነው፡፡ በሌላ በኩል መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚችል ሰፊ የሰው ሃይል ለማሰባሰብና ለመገንባት በቂ ዝግጅት ሳያካሂድ የሲቪል ሰርቪሱን የማሻሻያ ኘሮግራሙን በቁርጠኝነት ለማስፈፀም መቸገር ነው፡፡

መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በማደረገው ርብርቦሽ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም ህብረተሰቡን ሞብላይዝ ማድረግ የቁርጠኝነት ችግር መኖር፡፡ ሙስናን ለመዋጋት የሚደረገው እንቅስቃሴ በአብዛኛው አመራሩ እራሱ በሙስና ተዘፍቆ የሚገኝበት ሁኔታ ይታያል፡፡ የግብር ሥርዓት ማሻሻያው በተሳካ ሁኔታ እንዳይከናወን ግብር ከፋዩን በሙሉ ተገቢ ግብሩን እንዲከፍል ለማድረግ አለመቻል፡፡ መንግስት የሚወስዳቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች በወቅቱ በሰፊው በማብራራት ከህዝቡ የሚነሱ ሃሳቦችን ተቀብሎ

በቂ ማብራሪያ ሰጥቶ ለማስተካከል የቁርጠኝነት ችግር መኖር:: በአስፈጻሚው አካል የቁርጠኝነት ማነስ ምክንያት ያስፈጻሚው ችግሮች ጉልተው በመውጣት በህዝቡ ውስጥ ቅሬታ መፍጠሩ:: ጉቦ ሰጭና ተቀባዮቹ የኮንትሮባድን ነጋዴዎቹ ግብር ሳይከፍሉ ለመክበር ሞካሪዎቹ ወዘተ እነሱና መሰሎቻቸው በአመራሩ የቁርጠኝነት ችግር የተነሣ አሁንም ተስፋፍተው ይገኛሉ፡፡ስለዚህ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከአስፈጻሚ አካላት በርካታ ቁምነገሮች ይጠበቃሉ::

## 3.5. መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ያለው ሚና

በማቋቋሚያ አዋጁ እንደተገለፀው የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዜጎች ላይ የሚፈፀሙ የአስተዳደር በደሎች የሚወገዱበትንና የሚታረሙበትን መንገድ ለመሻት እንዲሁም የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ሚና በዜጐች የእለት ተእለት ሕይወት ጋር ያላቸው ቁርጠኝነት እየተጠናከረ በመምጣቱ ፍትሃዉነት የጎደላቸው ውሳኔዎች እንዳይኖሩ ቢኖሩም በወቅቱ እንዲታረሙ ወይም ጉዳት እንዳያደርሱ እንዲሁም አስተዳደራዊ በደል የደረሳባቸው ዜጐች ተጎድተው እንዳይቀሩ /በቀላሉ/ ቅሬታቸውን የሚያሰሙበትና መፍትሄ የሚሹበት ተቋም ለመፍጠር ታስቦ የተቋቋመ ነው፡፡ ይህም ሲሆን የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ስለህግ አውጪው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የሚቆጣጠር መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የተመሰረተ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ያየነው ህግ አውጪው ለምን ተቋሙን አንዳቋቋመ ምክንያቱን ያስቀመጠበትን ሲሆን የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዓላማ /የአንቀጹ የአገላለጽ ግድፈት እንዳለ ሆኖ/ የዜጎች መብቶች በአስፈፃሚው መከበራቸውንና የህግ የበላይነት መከበሩን ማረጋገጥ፤ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው አስተዳደር እንዲመሰረት በማድረግ መልካም አስተዳደርን ማስፈን ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ በአንቀጽ 6 ስር ሰፋ ያለ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ የተቋሙ የስልጣን ገደብ ሰፋ ያለ መሆኑን የምንረዳው ይህንን በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5 እና አንቀጽ 7 ጋር አዛምደን ስናየው ነው፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ ፍትህን በማስፈንና የዜጎች መብቶች መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ ሁለት አካሄድ አለው፡፡ የመጀመሪያው አካሄድ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የመንግስት ተቋማት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፡ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችንና አሰራራቸው የዜጎችን መብቶችና ህገ-መንግስቱን፣ ህጎችን /ለምሳሌ አዋጆችንና ደንቦችን/ የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ /አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1/ ሲሆን ተቋሙ በዚህ ረገድ ያለበት ሃላፊነት ሰፊ ነው፡፡ የአስፈፃሚ አካላት አስተዳደራዊ መመሪያዎች ከመጽደቃቸው በፊት ማየትና ተገቢውን አስተያየት መሰንዘር፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ረቂቅ ህጎችን አዘጋጅቶ ማቅረብን ይጨምራል /አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2/ሠ//፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የአስፈፃሚው አካል ስራውን በህግ መሰረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ /አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 3/ እንዲሁም የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ህጎች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፣ አዲስ ህጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ ስልጣን ተሰጥቶታል /አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀፅ 6/፡፡ ይህ ሰፊ ስልጣንና ኃላፊነት በሃገሪቱ በአጠቃላይ መልካም አስተዳደር ለዘለቄታው እንዲሰፍን ለማድረግ የሚያስችለው ሲሆን የስራውን ክብደትም የሚያመለክት ነው፡፡ የዚህ እንድምታም መልካም አስተዳደርን በስፋትና ለዘለቄታው ለማስፈን ተቋሙ የእያንዳንዱን የመንግስት ተቋም አሰራርና ደንብ በጥልቀት መመርመር እንደሚጠበቅበት ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ግዙፍ ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለተኛው በአዋጁ የተመለከተው የተቋሙ አካሄድ ደግሞ ተቋሙ አስተዳደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የመመርመር /አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2/ አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ያመነበት ከሆነ የመፍትሄ ሃሳብ የመሻት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተደጋጋሚ ከሆነ የመፍትሄ ሃሳብ የመሻት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተደጋጋሚ የአስተዳደር ጥፋቶች የሚከሰትባቸውን አካባቢዎችን ሁኔታዎች

አጥንቶ /አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 2/መ// የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የመፍትሄ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው /አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 5/፡፡

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም መልካም አስተዳደርን በማስፈን ረገድ የተለያዩ ስትርቴጂዎችን በስራ ላይ ማዋል ይኖርበት ይሆናል፡፡ ይህም የሚታየዉ በአገሪቱ ካለው ማህበራዊ ሁኔታ፣ ለተቋሙ የተሰጠው ስልጣን ኃለፊነትና ከመልካም አብተዳደር ፅንሰ ሃሳብ ተፈጥሮ ጋር የተገናዘበ ነው፡፡

መልካም አስተዳደርን በመንግስት አሰራር ውስጥ ለማስፈን የነቃ ህብረተሰብ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ህዝቡ ስለመልካም አስተዳደር መሰረታዊ እውቀት እንዲኖረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች መስራት እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምም አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በዚህ ረገድ ሰፊ ስራ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

ሕዝቡ የመልካም አስተዳደር ግንዛቤው ሲሻሻል ከመንግስት ተቋማት የሚጠይቀው ነገር አለው፡፡ የመንግስት ተቋማት ለዚህ ጥያቄ አግባብነት ያለው ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉት ይህንኑ ለማድረግ አቅም ሲኖራቸው ነው፡፡ ስለዚህ ለመንግስት አስፈፃሚ አካላት ተገቢውን የመልካም አስተዳደር ትምህርት መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

## ክፍል አራት

4. **የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ተግባሩን እንዲወጣ ከአስፈጻሚ አካላት ከመገናኛ ብዙሃን እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምን ይጠበቃል?**

### 4.1.ከአስፈጻሚ አካላት ምን ይጠበቃል

አስፈጻሚ አካላት ስልጣንና ተግባራቸውን በአግባቡ እንዲወጡ በርካታ ጠቋሚ ነጥቦችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡

- ልማታችንን በማፋጠን ድህነትን ማስወገድ የምንችለው ስትራቴጂዎችን ለመተግበር የሚያስችል የማስፈፀም አቅም ስንገነባ ነው፡፡
- የአቅም ግንባታ ሥራዎች ማከናወን ወሳኝ መሆኑ አንድ ጉዳይ ሲሆን የአስፈጻሚው አካል ቁርጠኝነት የላቀ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚቻልበት መሆኑ ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡
- ለዲሞክሲ ሥርዓት ማበብና ለመልካም አስተዳደር መስፈን እንቀሳቃሽ ሃይል/መሪ ተዋናኝ/ አመራሩ ነው፡፡ በሲቪል ሰርቪሱና በዳኝነቱ ሥርዓቱ ውስጥ ቢሆን የአመራሩ ቁርጠኝነትና ግንዛቤ  የላቀ ሚና ሊጫወት የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡
- በየትኛውም የደረጃ እርከን የሚገኘው አስፈጻሚው አካል የመንግስት ስትራቴጂና ፖሊሲዎችን መተግበር የህልውና ጉዳይ ነው የሚል ጠንካራ አቋም ይዞ ባጭር ጊዜ ውስጥ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በአፈጻጸም ላይ የታዩ የቴክኒካዊ ብቃት ችግሮችን ቀርፎ የመልካም አስተዳደርን ባህል በማንሰራራት ሂደት ከአስፈጻሚው አካል ብዙ ይጠበቃል፡፡
- የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ለሚያደርጋቸው አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች በተለይም ጥናቶችን ሲያካሂድና የምርመራ መረጃዎችን ሲፈልግ አስፈጻሚው አካል ትክክለኛና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት መተባበር ይተበቅበታል፡፡

የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ለአስፈጻሚ አካላት በአዋጁ የተቀመጡለት  ሃላፊነትና ተግባር በትክክል  መፈጸማቸውን ለመቆጣጠር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉም አካላት ቀና ትብብር እንደሚያሳዩ ይጠበቃል
ከመገናኛ ብዙሃን
ከመንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች

በዜጎች ላይ የሚፈፀመው አስተዳደራዊ በደል የሚቀጭበትን ወይም የሚታረሙበትን ቀልጣፋ አሰራር መዘርጋት ለሰናይ መስተዳድር መሰረት የመጣልን ወቅታዊ እርምጃ የሚጠይቅ ከመሆኑ ባሻገር ተቋሙ ስለ ህግ አውጭው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ በመሆን ከሚያገለግሉት መ/ቤቶች አንዱ የሆነው የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የመንግስታዊ በዲሞክራሲ

ግንባታና በመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እገዛና ቅንጅት እንደሚሻ ይታመናል፡፡

በዚህ መሰረት መያዶች በዜጎች ላይ አስተዳደራዊ በደሎች እንዳይፈፀሙና አስተዳደራዊ ጥፋት የተፈፀመባቸው ዜጎች ተጉድተው እንዳይቀሩ ቅሬታቸውን የማሰማት ባህልን እንዲያዳብሩና ብልሹ አሰራርን የማይሸከም ህብረተሰብ እንዲፈጠር ግንዛቤ በመፍጠር በኩል ከተቋሙ ጋር በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

- የአስፈጻሚ አካላትና ባለስልጣኖቻቸው የሚሰጧቸው ፍትሀዊነት የጎደሏቸው ውሳኔዎችን በወቅቱ እንዲታረሙ ወይም እንዳይደርሱ መያዶች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች ሁሉ ህብረተሰቡንና የሚመለከታቸውን አካላት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የተቀናጀ ስራ ለመስራትና ለሰናይ መስተዳድር መሰረት በመጣል አንፃር ከተቋሙ ጋር የቅርብ ግንኙነት መመስረትና የመረጃ ልውውጥ ማድረግ፡፡
- የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በቀጣይ ለሚከፍታቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ልምዳቸውንና ተሞክሯቸውን በማካፈል በኩል እገዛ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## *1.2 የእንባ ጠባቂ ዋና መለያ ባህሪያትና ዓለም አቀፍ ገጽታ*

### *1.2.1 የህዝብ እንባ ጠባቂ ዋና መለያ ባህሪያት*

እንባ ጠባቂ የአስተዳደር ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ የሚከላከልና ከተፈፀሙም እርምት እንዲወሰድባቸው የሚከታተል አካል ሲሆን የተለያዩ ፀሀፊዎች የሚከተሉትን የዕንባ ጠባቂ ባህሪያት አስቀምጠዋል፡፡

ዕንባ ጠባቂ፡-

9. ከመንግስት ተፅዕኖ ገለልተኛ ነው፣
10. የማያደላ መሆን አለበት፣

11.የአስተዳደር ስራዎችና የህዝብ አገልግሎቶች ቀልጣፋ በሆነ አኳኋን ፍትሃዊ፣ ምክንያታዊ እና ትክክለኛ በሆነ አኳኋን የሚሰጡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለው፣

12.ጽ/ቤቱን ለሁሉም ዜጐች ክፍት አድርጐ ማገልገል አለበት፣

13.ለሀገራዊ ደህንነት አስጊ ያልሆኑ ሚስጥራዊ ምርመራዎችን የማከናወን ችሎታ ያለውና ቅሬታ አቅራቢዎች እንዳይቀጡ የሚከላከል ነው፣

14.በመንግስት አስተዳደር የተካነ /እወቀት/ ያለው መሆን አለበት፣

15.ምርመራ የሚያከናውነው ፍ/ቤቶች ከሚከተሉት የህግ አሰራር በተለየ ነው፣

16.ለህግ አውጪው ምክር ቤት አመታዊ ሪፖርት የማቅረብ ግደታ አለበት፣

## *1.3 የእንባ ጠባቂ ተቋም ዓለም አቀፋዊ ገጽታ*

የእንባ ጠባቂ ተቋም በ1809 ለመጀመሪያ ጊዜ በስዊዲን አገር እንደተቋቋመ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ዓመትም ስዊዲን አዲስ ህገ-መንግስት ያፀደቀችበት አመት የነበረ ሲሆን የእንባ ጠባቂ ተቋሙ እንደተቋቋመ የፖርላማ እንባ ጠባቂ ወይም ፖርላሜንታዊ እንባ ጠባቂ በሚል ስያሜ ይታወቅ ነበር፡፡

## *የኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም*

### *2.1 የኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋም ለምን አስፈለገ?*

በኢፌዴሪ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቂቋሚያ አዋጅ ቁጥር 211/1992 መሰረት፡-

- የኢትዮጵያ ህዝብ ለፖለቲካ ስልጣን ባለቤትነት እንዲሁም ለህግ ልዕልና ባካሄደው ረጅም ትግል የከፈለው መስዋዕትነት በዜጐች ላይ በዘፈቀደ የሚፈፀሙ የአስተዳዳር በደሎች የሚቀጩበትን ወይም የሚታረሙበትን ቀልጣፋ አሰራር በመዘጋት ለሰናይ መስተዳድር መሰረት የመጣልን ወቅታዊ እርምጃ የሚጠይቅ በመሆኑ፣
- የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ከዜጐች የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያላቸዉ ቁርኝትና ከመብታቸው ጋር በተሳሰረ ሁኔታ የሚኖራቸው የወሳኝነት ስልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየሰፋ በመምጣቱ፣
- በዚህ ሂደት የመንግስት አስፈፃሚ አካላትና ባለስልጣኖቻቸው የሚሰጧቸውን ፍትህዊነት የጐደላቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ ማረም ወይም እንዳይደርሱ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

- አስተተዳደራዊ ጥፋት የተፈፀመባቸው ዜጐች ተጉድተው እንዳይቀሩ በቀላሉ ቅሬታቸውን የሚያሰሙበትና መፍትሄ የሚሹበት ተቋም የማግኘት ፍላጐታቸው መሟላት ያለበት በመሆኑ፣
- ህግ አውጪው በህዝብ ተወካይነቱ ህግ አስፈፃሚው አካል ተግባሩን በህግ መሰረት የሚያከናውንና የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የዜጐችን መብቶች የማይጋፉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣
- ይህንኑ መርህ ለማጐልበትና ስለ ህግ አውጪው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ በመሆን ከሚያገለግሉት ተቋሞች መካከል አንዱ የሆነውን የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋም፣ ስልጣኑንና ተግባሩን በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 55/1 እና 15 መሰረት የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ስልጣኑና ተግባሩ ተወስኖለት በአዋጅ ቁጥር 211/92 ተቋቁሟል፡፡

### *2.2 የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዓላማ ምንድን ነው?*

የተቋሙ ዓላማ በህግ የተደነገጉ የዜጐች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈፃሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ፣ የህግ የበላይነትን መሰረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልፅነት ያለው መልካም የመንግስት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡

### *2.3 የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት ምን ምን ናቸው?*

ተቋሙ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት አሉት፣

- አስፈፃፀሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና አሰራሮቻቸው የዜጐችን ህገ-መንግስታዊ መብቶችና ህጐችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፣
- አስተደደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የመመርመር፣
- አስፈፃሚው አካል ስራውን በህግ መሰረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እዳይፈፀሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ፣

- አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ያመነበት ከሆነ የመፍትሄ ሀሳብ የመሻት፣
- አስተዳደራዊ ጥፋቶች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የማጥናትና ሀሳብ የማቅረብ፣
- የተሻለ የመንግስት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ህጐች ወይም አሰራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ አዳዲስ ህጐች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ፣
- ከዓላማው ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን ስልጣንና ተግባራት አሉት፡፡

በአጠቃላይ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈፀሙ መከላከልና ተፈፅመው ሲገኙም የሚታረሙበትን /የሚሻሻሉበትን/ የመፍትሄ ሀሳብ የማቅረብ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## *2.4 የኢፌዴሪ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የማያስተናግዳቸው ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?*

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም፡-

- በማንኛውም ፍ/ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን፣
- በፌደራልም ሆነ በክልል ምክር ቤቶች የተላለፈ ውሳኔና በዋና ኦዲተር በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን፣
- በፀጥታ ኃይሎችና በመከላከያ ሰራዊት ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሰኔዎችን፣
- መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሀይማኖት ተቋማት ከግለሰቦችና ከውጭ ድርጅቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አያይም፡፡